www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.44
ADDIS ABABA 5th March, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፬/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ………………..ገጽ ፲፩ሺ፩፻፹፩

## Content

Proclamation No.1114/2019

Amendment of the House of Peoples' Representatives Secretariat Establishment Proclamation……………………….Page 11,181

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፬/፪ሺ፲፩

**የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት ህገ-መንግስታዊ እና ሕዝባዊ ተልዕኮን ታሳቢ ያደረገ ሙያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማረጋገጥ፣ ም/ቤቱ በሰላም ፣ በዲሞክራሲ እና በልማት የሚኖረውን አዎንታዊ ድርሻ መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የምክር ቤቱ ጽ/ቤት የብሮድካስቲንግ፣ የጥናት፣ የምርምር እና ሙያዊ ምክር አገልግሎቶች የመስጠት ሃላፊነት እንዲኖረው ለማድረግ የማቋቋሚያ አዋጁን ማሻሻል የሚጠይቅ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፮/፪ሺ፯ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፬/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 1114/2019

**A PROCLAMATION TO AMEND THE HOUSE OF PEOPLES' REPRESENATIVES SECRETARIAT ESTABLISHMENT PROCLAMATION**

**WHEREAS**, ensuring the professional and Administrative support to the House of Peoples' Representatives, taking in to account its Constitutional and public mission and is necessary to prop up the role of the House in the country's peace, democracy and development endeavors;

**WHEREAS**, in order to have the Secretariat the responsibility of delivering the services of broadcasting, research, study and professional advisory it has been found necessary to amend the establishing Proclamation;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby Proclaimed as follows.

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as" The House of Peoples' Representatives Secretariat Establishment Proclamation No.906/2015 Amendment Proclamation No. 1114/2019."

www.chilot.me



## ፪. ማሻሻያ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፮/፪ሺ፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፭ ከንዑስ አንቀፅ (፲) ቀጥሎ የሚከተሉት ንዑስ አንቀፆች (፲፩) ፣ (፲፪) ፣ (፲፫) እና (፲፬) ተጨምረዋል፣ ከንዑስ አንቀፅ (፲፩) እስከ (፲፬) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀፅ (፲፭) እስከ (፲፰) በመሆን ተሸጋሽገዋል፡-

"፲፩/ በተለያዩ የሙያ ዘርፎችና ጉዳዮች ላይ ለምክር ቤቱ እና ለአካላቱ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፣ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ይሰራል ፤

፲፪/ የምክር ቤቱን ስራዎች እና የምክር ቤቱን ስልጣንና ተግባር የሚመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ዜናዎችንና መዋዕለ ዜናዎችን የማሰባሰብና የማዘጋጀት እንዲሁም የተለያዩ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ፣ በድረ ገፅ እና በልዩ ልዩ ዘዴዎች ያሰራጫል ፤

፲፫/ ሌሎች መጥተው ትምህርት የሚወስዱበትና ግንዛቤ የሚጨብጡበት የራሱ የሆነ ሙዚዬም ኖሮት ለዚሁ በሚመድባቸው ባለሙያዎች ተግባሩን ያከናውናል፤

፲፬/ የምርጫ ክልል ውክልና እና የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤"

፪/ የአዋጁ አንቀፅ ፮/፩/ (ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) ተሰርዘው በሚከተሉት ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) ተተክተዋል፡-

"ሀ) አፈጉባኤው ዕውቀትና ችሎታ ያለው ገለልተኛና ባለሙያ ነው ብሎ የሚያምነውን ሰው ይሾማል፤

ለ) በዋና ፀኃፊው አቅራቢነት በአፈጉባዔው የሚሾሙ ሁለት ምክትል ዋና ፀኃፊዎች ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት የሚቀጠሩ ዳይሬክተሮች እና ሰራተኞች፤"

## 2. Amendment

House of peoples' Representatives secretariat office re-establishment Proclamation No.906 /2015 is hereby Amended as follows:

1/ The following new Sub-Articles 11, 12, 13 and14 are added after Sub-Article 10 of Article 5 of the Proclamation, and the existing Sub-Articles from 11 to 14 are renumbered as Sub-Article 15 to 18:

"11/ to give advisory service on various professional fields and issues to the House and its bodies; undertake study and research activities;

12/ to organize and prepare news on issues related to the activities, powers and responsibilities of the House as well as broadcasting various programs on radio, television, website and other means of transmission;

13/ the secretariat shall have its own Museum which can give lesson for others; and assign professionals for this duty;

14/ it gives professional support for constituency works and parliamentary diplomacy;"

2/ Article 6 (1) (a), (b) and (C) of the Proclamation are deleted and replaced by the following paragraph (a), (b and (C) :

"a) the Speaker shall appoint a Secretary General, which he believes a neutral, professional and competent;

b) two Deputy Secretary Generals to be appointed by the Speaker upon nomination by the Secretary General;

C) directors and employees to be hired in accordance with the employees' administration regulation to be issued based on this Proclamation;"

www.chilot.me



፫/ የአዋጁ አንቀፅ ፮/፪/ እና /፫/ ተሰርዘው በሚከተሉት ንዑስ አንቀፆች /፪/ እና /፫/ ተተክተዋል፡-

“፪/ ለአፈጉባኤው ተጠሪ የሆነ የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ክፍል ይኖረዋል፤

፫/ ምክትል ዋና ፀሐፊዎች እና ዳይሬክተሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ፀሐፊው ይሆናል፡፡”

፬/ የአዋጁ አንቀፅ ፮ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል ፡-

“፭/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱት የጽህፈት ቤቱ አካላት ደሞዝ፣ ጥቅማ ጥቅም እና አበል በምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡”

፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፯ (፪) (ለ) ተሰርዟል፡፡

፮/ የአዋጁ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡-

“ሐ/ የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤“

፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፰ ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡-

“፰. የምክትል ዋና ፀሐፊዎች ስልጣንና ተግባር

፩/ ምክትል ዋና ፀሐፊዎች በዋና ፀሐፊው ተለይቶ የሚሰጣቸውን ዘርፍ ይመራሉ፣ ያስተዳድራሉ፡፡

፪/ ዋና ፀሐፊው ለይቶ ካልወከለ በስተቀር ዋና ፀሐፊው በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ፀሐፊውን ተክቶ ይሰራል፡፡”

፰/ የአዋጁ አንቀፅ ፲፩ ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡-

3/ Article 6 (2) and (3) of the Proclamation shall be deleted and replaced by the following sub-articles (2) and (3):

“2/ the secretariat shall have Internal Audit and Inspection section accountable to the Speaker;

3/ Deputy Secretary Generals and the directors shall be accountable to the Secretary General ”

4/ Article 6 (5) of the Proclamation is deleted and replaced by the following SubArticle (5):

“5, the salary, benefits and allowances of those referred to in SubArticle (1) of this Article shall be decided by the Business Advisory Committee of the House.”

5/ Article 7 (2) (b) of the Proclamation is deleted.

6/ Article 7 (2) (C) of the Proclamation is deleted and replaced by the following paragraph (C):

“C) Employ and Administer the support staff of the Secretariat based on Employees’ Adminstration Regulation issued under this Proclamation;”

7/ Article 8 of the Proclamation is deleted and replaced by the following Article 8:

“8. Powers and Duties of the Deputy Secretary Generals

1/ The Deputy Secretary Generals shall direct and administer the sectors specifically assigned to them by the Secretary General.

2/ Unless the Secretary General specifically assigned, in the absence of the Secretary General the senior Deputy Secretary General shall represent the Secretary General.”

8/ Article 11 of the Proclamation is deleted and replaced by the following Article 11:

www.chilot.me



"፲፩.ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

፩/ ምክር ቤቱ የጽህፈት ቤቱን የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ያወጣል፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡"

፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"11. **Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The House shall issue Employees' Administration Regulation of the Secretariat.

2/ Business Advisory Committee of the House shall issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulation issued under this Proclamation

3. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force upon its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Abeba, on this 5th day of March, 2019.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**